# ትብብሩንም አልደግፍም ኢህአዴግን ብቻም አላወግዝም!!

ባለፈው እሁድ ዲሴምበር 17 ቀን በአምስተርዳም ከተማ በተደረገው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ እኔና አቶ አን
ዳርጋቸው ተገኝተን ስላደረግነው ገለፃ ኢትዮጋርድያን በተሰኘው ድህረ ገፅ የወጣው ሪፖርት የተባለውን ቁምነገር በመ
ዝለልና ያልተባለ ነገር በማተት ስለእኔም ሆነ ስለህብረታችን አቋም እጅግ የተሳሳተ መልእክት አስተላልፏል። ይህ ሪፖ
ርት ድህረገፁን እዛ በነበሩት ዜጎች ፊት ትዝብት ላይ የሚጥል ቢሆንም ያልነበሩ አንባቢዎችን ደግሞ ግራ ያጋባ በመሆ
ኑ የህዝባችንን የነፃነት ቀን ለማፋጠን ስንት አጣዳፊ ስራ ከፊታችን በተደቀነበት በአሁኑ ወቅት ለዚህ አጓጉል ዘገባ በአ
ጭሩም ቢሆን  መልስ ለመስጠት ጊዜየን ለማባከን ተገድጃለሁ።

ስለስብሰባው በቀረበው ሪፖርት ላይ አቶ አንዳርጋቸውም ዶ/ር ነገደም ''ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ''
የተባለውን ስብስብ ደግፈዋል ተብሏል። በመስራች ጉባኤው ላይ ከተገኙት የህብረቱ ልኡካን አንዱ በመሆን ይህንን ስ
ብስብ ገና ከጥንስሱ ተቃውሜዋለሁ። ያኔ ሳር ቅጠሉ ''የትግል አንድነት'' እያለ ይወተውት በነበረበት ወቅት ይህንን ግ
ፊት ለመቋቋም የፖለቲካ ድፍረቱና ሃገራዊ ራእዩ ኖሮን ''ለሃገራችን የሚበጃት ይህ አይነቱ ስብስብ አይደለም'' በማለ
ት የተቃወምን ሰዎች ዛሬ ይህ ስብስብ ለሃገራችን አንድነትም ሆነ ሚልዮኖች ለቆሙላቸው የግንቦት ድሎች መከበር
አላማ ምንም ፋይዳ እንደሌለው እንዲሁ ''ሳር ቅጠሉ'' እየተረዳ በሄደበት ወቅት እኔ ''የጧቱ'' ተቃዋሚ ለምን፣ እንዴ
ትና ምን እብድ ነክሶኝ ወደ ድጋፍ እንደምሸጋገር ጨርሶ የሚገባ ነገር አይደለም። በዚህ በአምስተርዳሙ ስብሰባም ላ
ይ በሌሎች ስብሰባዎችና በፓልቶኮች ላይ ካልኩት ሌላ ምንም ነገር አላልኩም። ንግግሩ በቪድዮም የተቀዳ ስለሆነ የ
ተባለ ሊካድበት ያልተባለ ሊጨመርበት አይቻልም።

ዛሬ የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የመሰባሰቢያና የጋራ ትግል አጀንዳ የግንቦትን ድሎች አስመልሶ
በእነሱ ላይ የመገንባት አጀንዳ እንደሆነ፣ የግንቦት ድሎች ስንል ደግሞ ኦሮሞው ለኦሮሞ፣ አማራው ለአማራ፣ ትግራዩ
ለትግራዩ፣ ክርስቲያኑ ለክርስቲያኑ ሙስሊሙ ለሙስሊም ሳይሆን ሚልዮኖች የሃማኖትና የብሄርን አጥር ሰባብረው በ
ፖለቲካ አቋምና ምርጫ ድምፅ የሰጡበት ሂደት እንደነበረ አስረግጬ ተናግሪያለሁ።

ስለግንቦት ድል ምንነት ሲያብራራ ዶ/ር ነገደ ''ኢትዮድያውያን ለዴሞክራሲ ያላቸውን ፍላጎትና ዴሞክ
ራሲያዊትና ነፃ አገር ለመገንባት ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳዩበት ሂደት እንደሆነ'' ተናግሯል ተብሏል። ሆን ተብሎ እኔን
''ለነፃነትና ለዴሞክራሲ'' እታገላለሁ ለሚለው ስብስብ ደጋፊነት ለማመቻቸት ካልሆነ በስተቀር ነገሩ እንደዚህ ተጎር
ዶ መቅረብ አልነበረበትም። ''ከነፃነትና ዴሞክራሲም'' ዘልቆ የግንቦቱ ምርጫ ህዝባችን የኢትዮድያን ዴሞክራሲያዊ
አንድነት ሃሳብ ''በሬፈራንደም'' ያፀደቀበት የሃገር አንድነት ድል እንደሆነ በአምስተርዳሙም ሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎ
ች ሁሉ ከማብራራት የተቆጠብኩበት ወቅት የለም።

ወደ ዩትሬክቱ ስብሰባ ስንሄድ ህብረታችን ለተሰብሳቢዎቹ በፅሁፍ ባቀረበው አቋሙ መሰረት የማንኛው
ም የታጋዮች ስብስብ አላማ የግንቦትን ድሎች ለማስመለስና በነሱ ላይ ለመገንባት መታገል መሆን እንዳለበት በግልፅ
ያስቀመጠው አቋም እንደነበረ ጠቁማያለሁ። ከዚያም የግንቦትን ድሎች ለማስመለስ መታገል ሲባል ለእነዚህ ህዝባችን
ሞቶ ተሰውቶ ላስመዘገባቸው የዴሞክራሲ፣ የነፃነት፣ የሃገር አንድነት ድሎች መቆም እንደሆነ ለማስረዳት ሞክሬያለ
ሁ።

ከዚህም በማያያዝ ትብብሩን ከመሰረቱት አምስት ድርጅቶች አራቱ በዚህ በግንቦቱ ትግልና ድል ምንም
ሚና እንዳልተጫወቱና እንዲያውም ''ማርጅናል'' እንደነበሩ ጠቅሼ ዩክትክት ስንሄድ አንዱ አላማችን እነዚህ ሃይሎ
ች ሚልዮኖች ወደሚሳተፉበት የትግል መድረክ እንዲመጡና ከ''ሜይን ስትሪም'' ትግሉ እንዲደባለቁ ለማድረግ እንደ
ነበረ በግልፅ ተናግሪያለሁ። ነገር ግን ''ግዛኝ ብየው ብሄድ ሊሸጠኝ አሰበ'' የሚል ተረት ተርቼ የትብብሩ መስራቾች
ጭራሹን እኛን ''ከሜይን ስትሪሙ'' ማለትም በሚልዮኖች አጀንዳ ለዴሞክራሲ፣ ለነፃነትና ለሃገር አንድነት ትግል ከ
ሚካሄድበት መድረክ ሊያወጡን እንደሞከሩና ይህም ተቀባይነት እንዳላገኘ ከስምንት ወር ጀምሮ በያለበት የምለውን
እዚህም አምስተርዳም ስብሰባ ላይ ደግሜዋለሁ።

ኦነግም ሆነ ሌሎቹ በግንቦቱ ህዝባዊ ተጋድሎ ያልተሳተፉና ዛሬ ግን በትብብሩ ውስጥ አብላጭ ድምፅ ይዘው የቀረቡት ድርጅቶች ያልነበሩበትን ትግልም ሆነ ድል ስለማጣጣላቸው ጉዳይ ያለኝንም አስተሳሰብ ወደ ታሪክ ተመልሼ ይህ አቋማቸው በየካቲት አብዮት ቅልበሳ ማግስት በዚህ ትግልና በድሎቹ ምንም ሚና ያልነበራቸው እንደ ህወሃት አይነቶቹ ጠባብ ብሄርተኞች ያስተጋቡ ከነበረው አቋም ጋር ያለውን ምስስል ለማሳየት ሞክራያለሁ። በየካቲት ማግስት የነህወሃት አካሄድ "የየካቲት አብዮት ብሎ ነገር የለም፣ የመሬት አዋጅ ተብሎ ደርግ ያወጀው የማደናገሪያ ጥገናዊ ለውጥ ነበር" ከማለታቸው ሌላ ማንኛውም የየካቲት ድል የተገኘው የኢትዮጵያ ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው ባደረጉት የጋራ ትግል መሆኑ ሲታወቅ እነሱ ግን "ከየካቲት በፊትም፣ በየካቲትም፣ ከየካቲት በኋላም" ዋናው በሃገራችን የነበረውና ያለው ቅራኔ የብሄር ቅራኔ ነው እያሉ ያራምዱ የነበረውን አጉል ቴወሪ ካወሳሁ በኋላ ወደ ዛሬው ሁኔታ ተመልሼ አንዳንድ ቁምነገሮችን አንስቻለሁ።

በግንቦቱ ትግል ሚና ያልነበራቸው እንደ ኦነግ ያሉ ሃይሎች አካሄዳቸው ከየካቲት ማግስቱ የወያኔ አቋም እንደማይለይ ለማሳየት አንደኛ በዩትሬክቱ ስብሰባ ላይ እኛ ዋናው የዛሬው ተግባራችን መስመር የሳተውን (ዲሬይልድ የሆነውን) የዴሞክራሲ ሂደት መልሶ በእግሩ ማቆም ነው ስንል አቶ ዳውድ ኢብሳ እንዴት "ዲሬይልድ የሆነ ፕሮሰስ የለም!" ብሎ እንደመለሰልን፤ ከዚያም በሃምሌ ወር በታተመ "ማለዳ" በተሰኘ መፅሄት የኦነግ ቃል አቀባይ አቶ ሌንጮ ባቲ የግንቦትን ምርጫ እንዴት "የኦሮሞ ህዝብ ያልተሳተፈበት" ሂደት ብሎ እንዳጣጣለው፣ ከዚያም በጥቅምት ወር ሌላ የኦነግ መሪ የሆኑት ዶ/ር በያን የካቲት ማግስቱን ወያኔያዊ አነጋገር በመቅለብ "የኢትዮጵያ ፖለቲካ የሚውጠነጠነው በብሄር ጥያቄ ዙሪያ ነው፣ ቅንጅትም ቢሆን ስሙን ቀየረ እንጂ የአማራ ድርጅት ነው!" ያሉትን ጠቅሸ ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የተባለው ስብስብ ለምንና እንዴት ለተያዘው "የግንቦትን ድል የማስመለስ" አጀንዳ የሚመጥን ስብስብ እንዳልሆነ አብራርቻለሁ። ይህ ሁሉ እንግዲህ እንደ "ድጋፍ" ከተወሰደ የሚያሳየው አንድ ነገር ቢኖር የዚህ ስብስብ ደጋፊዎች ከፍተኛ የሆነ የተቀባይነት ቀውስ ላይ ወድቀው የሚይዙት የሚለቁት እያጡ መሄዳቸውን ብቻ ነው።

በሱማሊያም ጉዳይ በስብሰባው ላይ "ሁለቱ ተወካዮች" የኢህአዴግን በሱማሊያ ጣልቃ ገብነት አውግዘው ኢህአዴግ በዚች አገር የውስጥ ጉዳይ ገብቶ "መፈትፈቱን እንዲያቆም" ጠይቀዋል ተብሏል። ይህ እውነት ነው። ነገር ግን አቶ አንዳርጋቸው በዚሁ ላይ ሲቆም እኔ ሌላም የጨመርኳቸው ነጥቦች ነበሩ። በዚህ እጅግ ውስብስብና ቁምነገር ያዘለ ጥያቄ ዙሪያ የሚካሄደው ውይይት በቁም ነገር እንዲካሄድ ቢፈለግ ኖሮ እኔ ከዚህ አልፌ ሄጄ የጨመርኳቸው የሸአብያንና የሱማሊያውን የእስላም ፍርድ ቤቶች ህብረት አቋም የሚመለከቱ መሰረታዊ ነጥቦች እንዳልነበሩ አድርጎ ከማለፍ ይልቅ እነ አቶ አንዳርጋቸው ስለሸአብያ አካሄድና ስለ ሱማሌ ፍርድቤቶች ህብረት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ጉዳይ ያላቸውን አቋም መጠየቁ ይበልጥ ጠቃሚ አካሄድ ነበር።

የሆነ ሆኖ በበኩሌ አስተያየት መስጠት የጀመርኩት ያለንበት ሁኔታ ለሃገራችን ሰላምም፣ ለዴሞክራሲም ለአንድነቷም በጣም አደገኛ ሁኔታ እንደሆነ በመጠቆም ነበር። ጀርመን ከሁለት ተከፍላ በነበረችበት ወቅት አንድ ፀረ ጀርመን የነበረ ፈረንሳዊ የፖለቲካ ሰው ተከፋፍላ መቆየቷን ለመደገፍ "ጀርመንን ስለምወዳት አንዲት ጀርመን ብቻ አትበቃኝም" ያለውን አነጋገር ጠቅሼ ዛሬም በኛ አገር ጉዳይ "ኢትዮጵያን ከመውደዳቸው የተነሳ አንዲት ኢትዮጵያ ብቻ የማትበቃቸውና" አራትም አምስትም አገሮች እንዲወጧት የሚሹ የቅርብም የሩቅም ሃይሎች እንዳሉ ጠቁሜ ነገሩን "የኢህአዴግን ጣልቃ ገብነት" በማውገዝ ብቻ በቀላሉ መሸኘት እንደሌለብን በግልፅ አስቀምጫለሁ።

ከዚያም በአካባቢያችን ቢያንስ የውስጥ ይዞታቸውን ለማጠናከር ሲሉ ጦርነት ከሚፈልጉ ሃይሎች ኢህአዴግ ላይ ብቻ ጣት መቀሰር እንደማያዋጣ ሸአብያም፣ የሱማሊያ የእስላም ፍርድ ቤቶች ህብረትም አደገኛ ፖለቲካ እየተከተሉ እንደሆነ በግልፅ አስቀምጫለሁ። በዚህ ብቻ ሳላቆም እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች የኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን የሸአብያም ሰራዊት ከሱማሊያ እንዲወጣ መጠየቅ እንዳለብን ተናግሪያለሁ። ከዚህ አልፌ ደግሞ ልክ ኢህአዴግ በሱማሊያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን ማውገዝ እንዳለብን ሁሉ የሱማሊያው የእስላም ፍርድ ቤቶች ህብረትም በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ መፈትፈቱንና በሃገራችን ላይ በይፉ ያወጀውን የግዛት ይገባኛል ጥያቄ ለምን በግልፅ ማውገዝ እንዳለብን አብራርቻለሁ። በስብሰባው ላይም በቅርቡ ከሱማሌ ተወላጆች ጋር በጋራ ሰልፍ የማድረግ እቅድ እንዳለ አንድ ተሳታፊ ሲገልፅ ይህ ሰልፍ የኢህአዴግን ጣልቃ ገብነት ብቻ ሳይሆን የሱማሌ የእስላም ፍርድ ቤ

ቶችንም በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ማውገዝ እንደሚኖርበት ሃሳብ አቅርቤ ይህ ካልሆነ ግን ከሱማሌ
ዎች ጋር ሆኖ የኢህአዴግን መንግስት ብቻ ማውገዝ ''በአንድ እጅ ለማጨብጨብ እንደመሞከር ይሆናል!'' በማለት ያ
ለኝን አስተሳሰብ በግልፅ ለተሰብሳቢው ገልጫለሁ።

ይህንን ካልኩኝ ዘንዳ ወደዚህ ስብሰባ ከመሄዴም በፊት ሆነ ከዚያ በኋላ ከአንዳንድ ወገኖች ዶ/ር ነገደ
ከአቶ አንዳርጋቸው ጋር ይፋ ስብሰባ መቀመጡ ህብረቱ በቅንጅቱ ውስጥ ባለው ክፍፍል አንዱን ወገን የሚደግፍ የሚ
ያስመስል በመሆኑም በዚህ ድርጅት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ይሆናል በሚል ቅሬታ ለአሰሙ ወገኖች አንድ ነጥ
ብ ላስቀምጥ። በዚህ ጉዳይ የኔንም የህብረቱንም አቋም በስብሰባው ላይ ተናግራያለሁ። የህብረታችን ምኞት ሁለቱም
ወገኖች ለዴሞክራሲና ለሃገራችን አንድነት እስከቆሙ ድረስ ያላቸውን ልዩነቶች በጥሞና ተወያይተው እንደገና ወደ አ
ንድነት እንዲመጡና ትግሉን በቅጡ እንዲያግዙ እንደሆነ፣ በዚህ ልዩነት ህብረታችን ይህንን ወይም ያንን ወገን ደግፎ
መንቀሳቀስ ጨርሶ እንደማይፈልግ ገልጫለሁ። የኔ በዚህ አቶ አንዳርጋቸው በተገኙበት ስብሰባ መገኘቴ ወገናዊነት የ
ማሳየት ጉዳይ እንዳይደለና ነገ እነ ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው የተጋበዙበት ጉባኤ ብጠራ ያለማመንታት እንደምሄድና የነሱን
ም አቋም ለማዳመጥም ሆነ የህብረታችንን ሃሳብ ለማሰማት ወደ ኋላ እንደማልል በግልፅ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ነው
።

**ነገደ ጎበዜ**
20/12/06